Title: Azmach Feseha Zewde, Sami Haji Aman, Tore Neguse, Azmach Kasa Woldeyohanes, and Teruneh Walde Interview

Creators: Zewde, Azmach Feseha; Aman, Sami Haji; Neguse, Tore; Woldeyohanes, Azmach Kasa, Walde, Teruneh; Bekele, Getnet

Date: August 20, 2010

City: Koshe

Country: Ethiopia

African Oral Narratives: aodl.org/oralnarratives

ዛሬ እዚህ የተሰባሰባችሁት እሳቸው ፕሮፌሰር ጌትነት በቀለ ይባላሉ ለምን እንደማጡና ከየት እንደማጡ ራሳቸውን በማስተዋወቅ ጀምረው ግብርናውን መሠረት ያደረገ ጥያቄዎች ያቀርቡላችኋል እናንተም የምታውቁትን በሙሉ በዝርዝር እንድትገልፁላችሁ በሀገር አቀፍ ደረጃ ህጋዊ የሆነ መረጃ ለማሰብሰብ ፈቃድ አግኝተው የማጡ ሲሆን በክልል ደረጃም ፈቃድ ተሰጥቷቸው ከጉራጌ ዞን የኛ ወረዳ የተመረጠ በመሆኑ ነው ወደዚህ የማጡት አሁን እሳቸውን ስሙቸው

እኔ ጌትነት በቀለ እባላለሁ የመጣሁት ከአሜሪካን ሀገር ነው ዓለም ባንክ አክላንድና ሚሺጋን ዩኒቨርስቲዎች የአካባቢ የአየር ሁኔታንና የአየር ብክለትን እንዴት መቋቋም እንችላለን እና የገበሬ የአኗኗር ሁኔታ በምግብ በእርሻ የሚለውን በተለያየ ሳይንሳዊ መንገድ ጥናት ቢደረግም የገበሬውን ሃሳብ ስላላገኘን ጥናቱ ሙሉ ስለማይሆን አሁን እናንተን ለማናገርና ጥናታችንን ሙሉ ለማድረግ ነው፡፡ እኔ ጥያቄዎች አቀርባለሁ እናንተ የምታውቁትን ከቀደመውም ጊዜ ጀምሮ አስከአሁን የምታውቁትን ታስረዱኛላችሁ፡፡

በቅድሚያ እኔ እንዳደረኩት ስምና ዕድሜያችሁን እዚህ አካባቢ ምን ያህል ጊዜ እንደኖራችሁ ትገልፁልኝና ጥያቄአችንን እንጀምራለን፡፡

1. አዝማች ፍስሀ ዘወዴ የተወለድኩት በድሮ ሸዋ ክ/ሀገር ሜታ ሮቢ ወረዳ ነው ከ1940 ጀምሮ እዚህ ሚኖር ነው የምኖረው

2. ሀጂ አማን ዕድሜ 38 የተወለድኩት ስልጢ ወረዳ ዶዶሎ በር የሚባል ቀበሌ ነው በህፃንነቴ በ1963 ዓ.ም ነው ከቤተሰብ ጋር ወደዚህ የመጣሁት ትምህርት ጀምሬ ነበር ሆኖም ብዙ አልገፋሁበትም አሁን በግብርና ነው እየተደደርኩት ያለሁት
3. ሜጡሬ ንጉሴ እባላለሁ የተወለድኩት ሰሜ ዲዳ ቀበሌ ነው በጋብቻ ነው ወደዚህ የመጣሁት ስምንት ልጆች አሉኝ የምተደደረው በግብርና ነው
4. አዝማች ካሣ ወ/ዮሐንስ የተወለድኩት ሶዶ ወረዳ ነው በ1946 ነው ወደዚህ የመጣሁት የምትዳደረዉም በግብርና ነው፡፡
5. ስሜ ጥሩነሽ ወልዴ የተወለድኩት ቡታጅራ ማስቃን ወረዳ ሲሆን በልጅነቴ ሚዜቆ ገብቼ እዚሁ ነው የምኖረው
6. ሚጋ አሰፋ የተወለድኩት በ1958 ነው የምትዳደረው በግብርና ነው እስከ 6ኛ ክፍል ተምሬ አለሁ፡፡

አሁን ራሳችሁን አስተዋወቃችኋል ወደ ጥያቄ እንገባለን፡፡

ጥ. የመጀመሪያ ጥያቄ ለአቶ አዝማች ፍስሀ አቀርባለሁ ለ60 ዓመታት እዚህ አካባቢ ኖሬአለሁ ብለዋል? እንዴት ነው እዚህ አካባቢ ምን አዲስ ነገር አለ ከድሮው ጋር እያነፃፀሩ ቢነግሩኝ?

መ. እዚህ አካባቢ ስኖር ብዙ ልጅ ወልጄ እስከ ቅድምአያት ደርሻለሁ ዘሬም እስከ 63 ደርሷል፡፡ ልጆቼ ግማሾቹ ተምረዋል የተወሰኑትም በግብርና ላይ ነው ያሉት፡፡

ከ1940-2002 ድረስ በእርሻና በተለያዩ ሥራዎች ነው የኖርኩት አብዛኛው ስራዬ እርሻ ነው አርሳለሁ አደግ ብዬ ወደ ደህና ሰዎች ለማጠጋት ስፈልግ ደርግ ብቅ ብሎ ትንሽም ያለዉ ብዙም ያለዉ ሜልጭ አድርጎ ወርሶ እኔም ያሉኝ ሜሬቶች ተወርሰው አደህሪ ነው ተባልኩ በዚህ ሁኔታ እያለን ኢህአዲግ ገባ በእኔ በኩል የነፃነት መንግስት ነው እለዋለሁ፡ ሀብት ባገኝም ባላገኝም ነፃነት አለ ችግርንም ለፈለጉት ባለስልጣን የማቅረብ መብት አለ ሜልስ ቢገኝም ባይገኝም በእርሻው ያለው ሁኔታ አሁን በጣም ጥሩ ነው በ2001 ዓ.ም. ድርቅ ነበር ዘንድሮ ከጥቅምት ወር ጀምሮ ዘነበ በግብርና ሠራተኞች ክትትል ጥሩ እሸትና ቃሪያ አግኝተናል የካቲት 19-23 የተዘራ ሽንኩርት ማጋቢት ግማሽ ላይ ደርሶ ተሸጧል መንግስት ወይም የአካባቢው ባለስልጣን ገበያ አፈላልጎ ባያገኝም በተባባሪ ነጋዴ ሽጠናል በተለያየ ዋጋ

ጥ. በዚህ ዓመት እርሻው ጥሩ የሆነው የዝናቡ ሁኔታ ማስተካከሉ ነው ብለዋል ይሄ ዋና ምክንያት ይመስልዎታል?

መ. ዋናው ዝናቡ ነው ምንም እርዳታ ቢደረግ ዝናብ ከሌለ ዋጋ የለውም

ጥ. በእርስዎ ዕድሜ የገበሬው የስራ ሁኔታ /ህይወት/ የሚወሰነው በመንግስት ፖሊሲ ነው ወይንስ በዝናቡ?

መ. የተለያየ ነው አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ይሰጣል በመንግስት መሟላት ያለባት ሳይሟላ ይቀርና ምርቱ ይቀንሳል፣ አንዳንደ ደግሞ በመንግስት የሚሟላው የሟላና ዝናቡ ይጠፋል፡፡ በእርግጥ የግብርና ባለሙያዎች በጣም ነው የሚረዱን እርሻችን ድረስ እየመጡ ነው እርዳታ የሚያደርጉልን፡፡

ጥ. እርስዎ እስኪ እንደት ወደ ግብርና እንደገቡ እና ባጠቃላይ ስለ ስራዎት ቢያስረዱኝ?

መ. እኔ በ1986 ነው እርሻ የጀመርኩት ወረዳችን በደህነት ተጠቃሽ ናት ህብረተሰቡ የግንዛቤ ችግር ነበረበት መንግስት እስከ መቼ ነው የሚረዳው በሚል አሁን ግብርና ሚ/ር ባለሙያም እየረዱን አየሩም ጥሩ ስለሆነ በደንብ እየሠራን ነው፡፡

ጥ. በፊት ተሜዬ ነበርክ ሜሬት ከቤተሰብ ነው ወይስ ከየት አገኘህ?

መ. አባቴ ሲያረጁ ትምህርቴን አቋርጨ አባትና እናቴን ለማኖር መጣው የነሱን እየሰራሁ ሳገባ ከአባቴ ተካፈልኩኝ በሜጨሻ አባቴ ሲሞቱ ሜሬቱን ጠቅልዬ ያዝኩኝ፡፡

ጥ. እርሻ የወንድ ነው ይባላለ በዚህ ሃሳብ እርስዎ ይስማሙ?

መ. አልስማም ሴቷ ብቻዋንም ከሆነች ለራሷ ታርሳለች፡፡ ባለቤት ካላትም አብራ ትሰራለች ስለዚህ የወንድ ስራ አይደለም፡፡

ጥ. ያላችሁበት ሜሬት የማንነው የእርስዎና የባለቤትዎ የጋራ ነው ብለው ያምናሉ ወይም የባለቤትዎ ብቻ?

መ. የጋራ ነው አሁንማ ዘመኑ ተሻሽሎ ወንዱም ሴቱም እኩል መብት አለው፡፡ የአባቴን ንብረት እንኳን ከወንድሜ ጋር እኩል እካፈላለሁ፡፡

ጥ. ሴት ልጅ አለዎት ካለዎት እንደርስዎ ይድሯታል?

መ. እንኳን የራሴን ልጅ በአካባቢው ያሉ ሴት ልጆች እንዳይዳሩ እመክራለሁ፡፡

ጥ. በዚህ አካባቢ በብዛት ማሳ ላይ በብዛት የሚዘሚተው ምንድን ነው?

መ. በዚህ አካባቢ ሜቴቱ ለምነው ስንዴ፤ በቆሎ፤ በርበሬ፣ ሽንኩርትና የመሳሰሉት ይሚታሉ

ጥ. የእነዚህ ምርቶች ዘራቸው ከየት ነው የመጣው?

መ. በርበሬ ከጥንት ጀምሮ ነው የሚቀ በርበሬ፣ የታወቀም ነው ሽንኩርት በቅርብ ነው የመጣው

ጥ. ሽንኩርት በደርግ ዘመን ነው የመጣው?

መ. በኢህአዴግ ነው

ጥ. በቆሎስ?

መ. እሱ ከጥንት ጀምሮ ነበር

ጥ. ከበርበሬና በቆሎ የቱ ነው የቀደመው ይባላል?

መ. እኩል ናቸው

ጥ. ስንዴስ?

መ. ስንዴ አዳስ ገበዎቹ ናቸው ያስፋፉቱ በፊት ብዙም አይሚት ነበር አሁን ጥቅሙ ስለታወቀ በስፋት ይሚታል

ጥ. ማሽላ እዚህ አካባቢ ተሚርቶ ያወቃል?

መ. ማሽላ ሁለት ዓይነት ነው ያለው ዘንጋዳ ድሮም ይዘራል

ጥ. ድሮ ሲሉ ከበቆሎ ጋር እኩል ነው?

መ. አዎ እኩል ነው

ጥ. ለምን ይመስልዎታል ሰው አንዱን አዝመራ መርጦ የሚዘራው እርሱ ስለሚዘሩት እህል ያስባሉ?

መ. አዎ አስባለሁ ለምሳሌ በርበሬና ሽንኩርት በክረምት ገንዘብ ሚጨምሬ ስለሆነ ለገንዘብ ተብሎ የሚዘራ ነው፡፡ ስንዴ ለሁለቱም ለቀለብና ለገንዘብ ተብሎ ይዘራል በገንዘቡ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ይሟበታል በአብዛኛው ግን በቆሎና ስንዴ ቀለብ ነው፡፡

ጥ. ሴት በሚሂሷ ይስማሙ?

መ. አዎ ሞፌርና ቀንበር ባልይዝም ገበሬዬን ተከትዬ እኮተኮታለሁ አርማለሁ እንዲያወም ከ4 ዓመት በፊት ሌላ ቦታ ለወዝ ተከለው አይቼ ገዝቼ አምጥቼ ዘርቼ ስከታተል ማገደኛው እየማዘዙ አወጥተው ጨረሱት፡፡

ጥ. እንዴት ሞከሩት በአካባቢው አለ?

መ. አዎ ያሚተ አለ የኔም የተወሰነ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ልጆቹ /እረኞቹ/ ማዘው አወጥተው አበላሹብኝ፡፡

ጥ. የተወለዱት እዚሁ አካባቢ ነው?

መ. ቡታጅራ ነው የተወለድኩት፡፡

ጥ. አካባቢውን ከልጅነትዎ ጀምሮ የሚያውቁት ከሆነ ምን የተቀየረ ነገር አለ?

መ. ውሃ ከወንዝ ነበር በእንስራ የምናመጣው አሁን በየደጃችን ሆኖልናል

ጥ. እርሻወስ ላይ ምን ለውጥ አለ?

መ. ብዙ ለውጥ አለ ድሮ የሚዘራው ትንሽና አልፎ አልፎ ነው ከብት ነበር የነበረው አሁን ሜዳቱ በሙሉ ታርሶ አንድ ቦታ የለም ከብትም የለ

ጥ ይሄ ሊሆን የቻለው በምን ምክንያት ነው? ሰው ከብት ሚርባት ለምን ተወ ውተት ስላልፈለገ ነው ሜዳቱ በሙሉስ ለምን ታረሰ በምን ተገዶ ነው?

መ. ከከብት ጥቅም የእርሻ ጥቅም ስለሚበልና የቦታ ጥበትም ስላለ ነው

ጥ. ከብት የነበረበት ዘመን ላይ ደርሰዋል?

መ. አዎ ደርሼበታለሁ የአባቴን አግኝቻለሁ

ጥ. አባትዎ ምን ያህል ከብት ነበራቸው?

መ. 55 ነበራቸው

ጥ. እርስዎ ምን ያህል ከብት አለዎት?

መ. አባቴ ሲሞቱ ሃላፊነቱ ወደ እኔ ዞረ የእናቴን ከብት እያገደኩ እናቴን እጦር ጀመር 1 ሄክታር ሜትም አለኝ

ጥ. ምንድነው ማሳዎ ላይ የሚዘሩት?

መ. በርበሬ ነው ለኔ ትልቅ ጉልበት የሰጠኝም በርበሬ ነው ብዬ መናገር እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ስንዴ ሽንኩርት እተከላለሁ፡፡ ሰንዴ ምርጥ ዘር እዘራለሁ ከቀለብ አልፌ እሸጣለሁ፡፡

ጥ. አሁንስ በርበሬ ይተከላሉ ትተዋል?

መ. አዎ ትቻለሁ፡፡ በሽታ ገብቶ ከተበላሸ በኋላ

ጥ. እዚህ አካባቢ ጭራሽ እርሻ አልነበረም ነበር ይባላል ይሄ እውነት ነው?

መ. አዎ ከብት በነበረበት ዘመን አልፎ አልፎ ነው የሚዘራው እንጂ እርሻ ዋና ስራቸው አልነበረም በርበሬ ብቻ ነው የሚተከለው አካባቢው በጣም ደን ነበረው አሁን የደኑ መመንጠር ይመስለኛል የአየር ሁኔታው የተቀየረበት

ጥ. ደኑ በብዛት ምን ዓይነት ነበር?

መ. ግራር ሀረግ የሚመስልና የተለያየ ነበር

ጥ. ደኑ የማን ነበር?

መ. የሠፈረው ህዝብ ነው የኛ ነው ብሎ ይንከባከበው ነበር ይጠበቅ ነበር መንግስት ብዙም ትኩረት ስላልሰጠና ስለሚዩከታተል ተጨፍጭፎ አለቀ

ጥ. ማን እየፈቀደ ነው ደኑ እየተጨፈጨፈ አዝርዕት ከተዘራ የጋራ የነበረው የግል ሆነ ማለት ነው ይህንን ማን እየፈቀደ ነው?

መ. በደርግ ጊዜ በወቅቱ የነበሩት ባለስልጣን ወይም የቀበሌ ሜዎች ናቸው የሚሰጡት ከቀበሌ አሜር ከተስማማ እነርሱ ናቸው የሚሰጡት 8 ሄክታር ድረስ ይሰጥ ነበር፡፡ ያኔ ለእርሻ ትኩረት አይሰጥም ነበር፡፡ አንዱ ሥርቶ ወጠቱ ሲታይ ሌላውም ይሰጠኝ እያለ የፈለገውን ያህል ሄክታር እየማጠረ ይወስድ ጀመር

ጥ. ስለደርግና ኢህአዲግ አወፎተናል ስለ አፄ ኃ/ስላሴ ትንሽ ቢነግሩን?

መ. ጣሊያን ወጣ አፄ ኃ/ስላሴ ተመለሱ በዛን ጊዜ የባላባት አስተዳደር ነበር በዛን ሰዓት ባላባቶች ጭቃሹምና ጭሰኞች ነበሩ ያን ጊዜ እንዲያውም የጭሰኛ ጭሰኞችም ነበሩ፡፡ በዚያን ወቅት አንድ ጋሻ ሜሬት የነበራቸው ከዘር የተወረሰ ወይም መንግስት የፈቀደው የወል /የመንግስት/ ሜሬት ይበዛል ያልታረሰው ሁሉ የመንግስት ነው የሚባለው ሚሪቆ እኔ ከገባው ጊዜ ጀምሮ ዝም ብሎ ሜሬት ይሰጠኛል አርሼ እበላለሁ ሰዎቹ በጣም ጥሩ ስለሆኑ ምንም ሳልከፍል አርሼ እበላ ነበር እየቆየ ሲሄድ እርቦ መጣ አንድ እጅ ለባለ ርስት እንሰጥ ጀመር፡፡

ጥ. እርቦ የሚባው መቼ የተጀመረ ይመስሎታል?

መ. ጣሊያን ወጥቶ ከ10 ዓመት በኋላ አካባቢ ይሆናል እርሶ የመጣው ከእርቦ ጋር ደግሞ አስራት መጣ ፡፡ አስር አርሼ ቢሆን 6ቱ ለራሴ ሶስት ለባለ ርስት አንድ ለመንግስት ማለት ነው ይሄን ሰጥተን ያለምንም ጭቅጭቅ አርሰህ እኖራለህ፡፡ እርሻም በብዛት አልነበረም ለምሳሌ ቀኛዝማች ሸቤ የሚባሉ ከ300 በላይ ከብት ነበራቸው አብዛኛው ህዝብ ከብት ነበረው ከብት በፈለገበት ተሰማርቶ ወሎ ሚታ ይገባል፡፡ እኔ ቦታ ላይ መጣ ብሎ ሜጨቃጨ የለም ምንም ችግር አልነበረም እርሶ ለምግብ ያክል ብቻ ነበር ብዙም ሽያጭ የለ በ1942 ዘንጋዳ ልትሸጥ ወጥታ አልሸጥ ሲላት እዛው ትታ የሄደች አስታውሳለሁ፡፡ በአፄ ኃ/ስላሴ በጣም ጥጋብ ነበር ደርግ መጣ ባላባት ተባረረ ሜሬት ተከፋፈለ ከዛ በኋላ ሜሬት እየተሸነሸነ ተሰጠ በዛ ነው የእርሻ ጣፉጫት የተጀመረ፡፡ ቀጥሎ ኮታ የሚባል ነገር መጣ እኔ ለመሻሻል በጣም ስለምሥራ ያልዘራሁትን 2 ኩንታል ጤፍ ተመደበብኝ አንድ ፈረሱላ በርበሬ ለዘማች ተብሎ ሁለቱንም ጤፍም አልዘራሁም በርበሬም አልተከልኩም ስለዚህ 4 ጆንያ ስንዴ ይዤ ሄድኩኝ ይህንን አንቀበልም ብለው እምቢ አሉኝ ከዛ ሌሎች ትተህ ሂድ አሉኝ ልሄድ ስል የወረዳ ሃላፊው መጥቶ አገኘሁት እና ያመጣሁትን ኮታ ስንዴ

አልቀበልም አሉኝ ስል የቀበሌው ሊ/መንበር ተጠየቀ ያልዘራውን ለምን አምጣ አልከው ተባለ የሚደበው ሌላ ነው አለ ከዛ ኮታም ሳልሰጥ ስንደዬን ይዜ ተመልሻለሁ በደርግ ያስመረረን ነገር ኮታ ነበር፡፡

ጥ. በደርግ ጊዜ ኮታ የሚባል ነገር መጥፎ ሰው መሟሩን ሰምተናል በኢህአዴግ ጥሩውን ሰምተናል መጥፎ የሚባል ካለ ቢነግሩን? እርስዎ እርሻ የጀመሩት በ1986 ስለሆነ

መ. መጀመሪያ ህዝቡ በደርግ ተሠቃይቶ የደከመ ነበር በደርግ ግን እፎይታ አግኝቷል በአሁኑ መንግስት መብት አግኝቷል ህዝቡ የያዘውን መሬት እንደያዘ ነው ያለው ገበሬው ባለመሟሉ የተፈጠረ ችግር እንጂ ምንም በደል አልደረሰም፡፡

ጥ. ሴቶች መብታቸውን አውቀው ተቀይረዋል ይባላል አሁን በትክክሉ ግን እርስዎ በቤትዎም በአካባቢዎም ያሉ ወንዶች ለሴቶች ያላቸው አመለካከት ተቀይሯል ብለው ያስባሉ?

መ. የግድ ይቀየራሉ እኛም ስንተገብርና ገብተን ስናስረዳም የግድም ቢሆን እየተቀየሩ ነው፡፡

ጥ. ለምሳሌ የእርስዎ ባለቤት እኩል ነን ብለው ያምናሉ?

መ. አዎ በፊት ነበር እንጂ አሁን እኩል ነን ብሎ ያምናል

ጥ. ሴትና ወንዶች ልጆቻችሁን እኩል ነው የምታሳድጓቸው?

መ. አዎ እኩል ነው ትምህርት ይማራሉ ያው ሴቶች ልጆች ለወላጆቻቸው ስለሚያስቡ እና በአንዴ ስለሚይለቅ እንጂ እኛ እኩል ነው ሁሉንም ለማድረግ የምንሞክረው፡፡

ጥ. በቤት ባለ ገንዘብ ወይም አምርታችሁ ከሸጣችሁ በኋላ በገንዘቡ ላይ እኩል የማዘዝ መብት አላት ሴቷ?

መ. አዎ ከዚህ 4 ዓመት ወዲህ እኩል ነው የምናዘው

ጥ. እርስዎ ስለጣሊያን ያውቃሉ ደርሰውበታል እንዴ?

መ. አይ እኔ አልደረስኩበትም አባቶቼ ሲያወሩ ከሰማሁት ጎጎቲና ሀሜክ ገበያ ሰፍረው እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡

ጥ. እርሻ ጣሊያን ነው እንዴ የጀመረው?

መ. አይ በአስተዳደር እንጂ በእርሻ እንኳን አልሰሩም

ጥ. ጣሊያን ግብር ማስገበር ጀምሮ ነበር እንዴ?

መ. አናውቅም

ጥ. ከጣሊያን በኋላ የባላባት ስርዓት ነበር ተብሏል? ከነበረ እስኪ ምን ዓይነት አስተዳደር እንደነበር ስለባላባቱ ቢገልፁልኝ ስማቸውን ካወቋቸው?

መ. ባላባቶቹ ቀኛዝማች ሸሸቤ አባታቸው ሜሴ ባከሙ ይባላሉ ባላምባራስ አሰፋ ባላባት ሆኑ ጭቃ ሹሞች ሽብሩ ዳጌ ስዩም የሚባሉ ነበሩ ዋናው አስተዳደር ባላባት ነበር፡፡

ጥ. ይሄ ስልጣን መጀመር እንዴት መጣ በዘር ነው ወይንስ በሹመት?

መ. በዘር የመጣም ነው ግን ከአንዳንድ አባቶች ስንሰማ አፄ ምኒልክ የወላይታ ዘመቻ የሄዱ ጊዜ ብርቆምን ከኔ ጋር ዘመቻ ሂድ በማለት አብረው ሄደው ሲማለሱ በዛው ሾሟቸው፡፡ ከአዋሽ በፊሰሰ ጂዶ በማለሰ የአቶ ብርቆም ንጉሴ ነው ተብሎ ሠጧቸው ይባላል፡፡ አፄ ምኒልክ የተለያየ የሆነ የሀገር መንግስት ነበር የጅማ አባ ጅፋር እንደሚባለው በየጎሳወና በየአርበኛው ይመራ ነበር፡፡ አፄ ምኒልክ አንድ ኢትዮጵያ ለማድረግ በጀመሩት ወታደራዊ ዘመቻ አርበኛው የራሱ ጦር ስለነበረው ወደኔ ተቀላቀል ሲሉ አልቀላቀልም ስለሚል በመዋጋት በማሸነፍ ወደራሳቸው ይቀላቅሉና የራሳቸውን ሰው ይሾማሉ በዚህ ነው ብርቆማ የተሾመት እነ ሻቃ በቀለም የማጡት ሚኪቆም በዛን ወቅት አልቀላቀልም ብላ የነበረች ሀገር ናት አዛዥ ለጤ የሚባሉ እምቢ ብለው ተዋግተው ተሸንፈው ወደ ሲልጢ ሄዱ ሚኪቆንም ወደ ስርዓቱ ጠቀለሉ፡፡

ጥ. በዛን ወቅት የነበሩት ባላባት ማን ነበሩ?

መ. በአዛዥ ለጩ ቦታ ብርቆሞ ተተካ ብርቆም ባላባት ሆኖ ሲኖር እንደገና ወደ ወላይታ ያልፉና ንጉስ ጦና ይህንን መንግስት አልቀበልም በማለታቸው የጦናን ፈረሰኝ ማሸነፍ የሚችል ማነው ተብሎ ሲፈለግ ሚኪቆ ነው ስለተባለ ምኒልክ ሲማጡ ብርቆም ሞቶ ልጃቸው ሚስቦ ሲያስቀብር ይደርሳሉ ሚስቦ ከአባታቸው ቀብር ላይ የባላባትነት ሥልጣን ተሰጥቷቸው ወላይታ ለጦርነት ከአፄ ምኒልክ ጋር ሄደው የወላይታን ሜሬ አሸነፉ ሽልማት ተሰጥቷቸው ተሾሙ

ጥ.	ሚኪቦ ፈረስ ነበራቸው?

መ.	ሚኪቆ በፈረስ ታዋቂ ነው ያኔም የተዋጉት በፈረስ ነው፡፡ የሚኪቆ ሕዝብ ተዋግቶ ራሱን የሚያስከብር ህዝብ ነበር፡፡

ጥ.	የሚኪቆ ሕዝብ ከሀድያ ጋር ይቀራረባል?

መ.	አዎ ነገዳቸው አንድ ነው

ጥ.	ከሰልጢ ጋርስ?

መ.	መጀሜያም ነገዱ ከሀዲያ ነው ትወልዱ የቦዬና የሚጎ ልጆች ናቸው የሚባለው

ጥ.	ሀሰን ኢንጃሞ የሚባል ሰው ታውቃላችሁ?

መ.	አናውቅም

ጥ.	ከሚኪቆ ለየት ብለው የሚኖሩ ምሁር አካባቢ አሉ እነሱ ምንድናቸው ዘራቸው?

መ.	ቀቤናዎች ናቸው እነሱም የሚኪቆ ዘር ናቸው

ጥ.	የባላባቶች ጥቅማቸው ምንድነው ደመወዝ አላቸው ወይስ ሚሴት ይሰጣቸዋል?

መ.	ጭቃ ሹም ይሾማሉ የመንግስት ግብር ይሰበስባሉ ባጠቃላይ ኃላፊነት አለባቸው

ጥ.	እንደ ዛሬ ሹመኞች ልንወስዳቸው እንችላለን?

መ.	አዎ ባላባቱ ከስሩ ጭቃሹም ጭስኛ ስላለ ከላይ ሆኖ ይህንን ያስከብራል ማለት ነው ሜሬትም ከሌላው በላይ ይዞታ አይዘም ለአርበኞች ሜሬት ሲታዘዝ ይሰጣሉ የተያዘና ያልተያዘው የሚያውቁት እነሱ ነበሩ፡፡

ጥ.	ከንሴቦ በኋላ ባላባትነት ቀረ ወይስ ቀጠለ?

መ.	የንሴቦ ቀጥሎ አሸቤ ነበሩ

ጥ.	እሳቸው ባላባት ሆነው ነው ደርግ የገባው?

መ. ከአሳቸው በኋላ ልጃቸው ቦታውን ይዘው እንዳለ ነው ደርግ የገባው

ጥ. ቱኬ ማማ ስለሚባል ሰው ምን ታውቃላችሁ?

መ. ቱኬ ማማ የጅዶ ኮምቦልቾ ባላባት ነበሩ ኦሮሞ ናቸው፡፡

ጥ. ሴቶች በአሁኑ ወቅት መብታቸው እየተረጋገጠና እየተከበረ መጥቷል እያልን ነው በእርስዎ ግምት ወንዶች ተሻሽለዋል?

መ. አዎ ተሻሽለዋል ተቀይረዋል ወንዱም የሴትን መብት እያከበረ በማጋገር ነው ሁሉም የሚደረገው ወንዱ እንደ በፊቱ በስልጣኑ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡

ጥ. ቅድም ሜዳ አለኝ ብለውኛል ያንን ሜዳ በፈለጉ መሸጥ ይችላሉ?

መ. አልችልም ሜዳ የመንግስት ነው መሸጥ መለወጥ አይቻልም

ጥ. መንግስት ሜዳቱ የራስዎት ነው እንደፈለጉ አድርጉ ቢባሉ ደስ ይሎታል?

መ. አይለኝም

ጥ. ለምን?

መ. ሜዳቴን ሸጬ የት እገባለሁ አልሸጥም ሜዳ የመንግስት ነው ይባል እንጂ ምንም የወሰደብኝ ነገር የለም እንዲያውም አስፈላጊ ነገሮችን እያሟላልኝ ነው መንግስት

ጥ. እርስዎ ጥቅሙን ስላወቁት አይሸጡም መብቱ ቢኖርስ ሰው ይሳሳታል ብለው ያስባሉ?

መ. ሁሉም የሜዳ ጥቅም ስለገባው አይሸጥም

ጥ. ሜዳቴ ይወሰድብኛል ብለው ሰግተው ያውቃሉ?

መ. በፍፁም ሰግቼ አላውቅም

ጥ. በደርግ ጊዜ እየተለካ የተወሰነ ይወሰድ ነበር ትርፍ ነው እየተባለ ይሄ አያሳስብም?

መ. አያሳስበኝም የያዛችሁትን እንደያዛችሁ እርጉ ተብለናል የሚከበው ስለግብር ብቻ ነው እንጂ ምንም አላስብም፡፡

ጥ. የሰሙት ነገር ካለ በሚሉ ወይም በከፊል ሚዚስ አቅቶት መሬት የተወሰደበት ካለ?

መ. የለም በፊት በደርግ ጊዜ መሬቱን ለራሱ አድርጎ ጦፍ ያሳደረ ሰው ይወሰድበት ነበር አሁን ግን እንድናለማ ብቻ ነው የምንቀሰቀሰው የምናመርተው ምርትም የራሳችን ነው መሬት ሳያርስ አንድ ዓመት ያሳለፈ ካለ መሬቱ ይነጠቃል የሚል መመሪያ ስላለ የማያርስ ገበሬ የለም

ጥ. ምን ያህል እርዳታ ታገኛላችሁ? ይጠቅማል ወይ እርዳታውስ አስፈላጊ ነው ወይ?

መ. ምናልባት እርዳታ ማለት ለህይወት ደራሽ ነው በጣም አርጅተው ጧሪ ለሌላቸው እንጂ እርዳታው ወሳኝና የምንተማመንበትና ቀጣይ መሆን የለበትም ህብረተሰቡም ወደ አቅመ ደካማ ስደተኛ እያደረገው ነው እርዳታውን ጠባቂ መሆን የለበትም የትምህርት ክህሎት ማሳደግ በዚህ መልኩ ቢሰጥ ነው፡፡

በሶስትና በአራት ዓመት በሚያጋጥም የአየር መዛባት የማረሻት አቅም የማያንሳቸው ሰዎች ማጠባበቂያ ቢሆን እንጂ ለሚሠራው ህዝብ ያስፈልጋል የሚል እምነት የለንም የአየሩ ሁኔታ ጥሩ በመሆኑ ዘንድሮ በግንቦት በቆሎ በልተን አሁን ስንዴ ዘርተናል በዚህ ሁኔታ ሚዳት የለብንም 2003 ዓ.ም.በዚሁ የአየር ሁኔታው ከቀጠለ እህል በጣም ነው የሚከሰው ዘንድሮ ሽንኩርት ሽጠን ስንዴ ዘርተናል ችግራችን የአየሩ ሁኔታ ነው፡፡ በግብርና ስትራቴጂም ድጋፍ እየተደረገልን ነው በዚህ 4 ዓመት ወስጥ በሞተር አልምተው ትልቅ ደረጃ የደረሱ አሉ፡፡ ሞተሩ ለሁሉም ከተዳረሰ ያለዝናብ የማምረት አቅማችን ከተሟላ እርዳታ አያስፈልገንም

ጥ. በ2001 ድርቅ አንደነበር ነግራችሁኛል እስኪ በዛን ጊዜ ስንቶቻችሁ እርዳታ አገኛችሁ?

መ. በ2001ዓ.ም. ባለመሟቱ በ2002 ዓ.ም ችግር ስለነበር እኔ ቤተሰቤ 10 ነው ግን በ3 ቤተሰብ ተብሎ ትንሽ ነገር ተሰጥቶኛል ስጦታው በቂ አይደለም፡፡ ዘንድሮ በበቂ ስላመረትን አርዳታም አንፈልግም

ጥ. የመሬት እጥረት አለብን ብላችሁ ትገምታላችሁ?

መ. ያለኝ አለኝ ያንሰኛል ብልም ከየትም አይገኝም የሌላቸውም በኮንትራት ይዘው የሚጠቀሙ አሉ ግን በአግባቡ ከሠራን ሜሬት አያንስም፡፡ ሜሬት ወደሶስት ዓይነት ነው ያለው በደርግ ጊዜ ባለስልጣን የነበሩ በስፋት ይዘዋል እስከ 40 ጥማድ የያዘ አለ ከ1982 ጀምሮ ትዳር የያዙና በደርግ ጊዜ ወጣት የነበሩ ምንም ሜሬት የሌላቸው አሉ ስለዚህ በራሱ ሜሬት ያሚተወን ለራሱ የሚጠቀም ከሆነ ሜሬት ያንሳል እኛ አሁንም ባለን ላይ በኮንትራት ጨምረን ይዘን ነው የምንሠራው ኮንትራት ማጠት ከቀረ እኛ በጣም እንቸገራለን ቀድመው የያዙ ናቸው ተጠቃሚ የሚሆኑት፡፡

እንዲሁም ልጆቻችን ሜሬት የሚከፈሉት ከቤተሰብ ነው ትምህርት ከ8ኛ ክፍል በላይ ቡታጅራ ሄደው ስለሆነ ይማሩ የነበሩት ያንን ሚድረግ ቤተሰብ ስለሚይችል ወደ ግብርናው ይመለሳሉ፡፡ አሁን ግን እስከ አስረኛ እዚሁ መማር ተጀምሯል፡፡ ስለዚህ ከግብርና ውጭ ለሌት አማራጮችን ይፈልጋሉ እንጂ ሜሬት እጥረት አለ፡፡

ሜሬት በጣም እየጠበበን ነው እኔ ያለኝ ቤተሰብ ከነልጅ ልጅ 63 ነው ያለኝ ሜሬትም 3 ሄክታር ነው ልጆቼም 8ኛ ና 10ኛ ክፍል እየጨረሱ እቤት የተቀመጡ አሉ እነዚህ ሜሬት ወይም ሌላ ስልጠና አግኝተው ሥራ ካልሰሩ በቤተሰብ ላይ ጫና ናቸው ስለዚህ ሜሬት በብዛት የያዙም ስላሉ የማስተካከል ስራ ቢሠራ የሚል ሃሳብ አለን፡፡

ቅድም እንደተባለው 5 ጥማድ ያለ አለ 50 ጥማድ ያለው አለ እነዚህ ሰዎች ግን 5 እና 4 ሚስት አላቸው ከእያንዳንዱ ሚስት 9 እና 10 ይወልዳል ስለዚህ እነዚህ ሰዎችም አከፋፍለው ባዶ እጃቸውን ነው ያሉት ስለዚህ ስራ መፍጠሩ ነው ጥሩ፡፡

ጥ. ስለ ቱኬ ማማ የሚያውቁትን ቅድም እናገራለሁ ስላሉ ቢነግሩኝ?

መ. ቱኬ ማማን አውቃለሁ ከቀኛዝማች ሽቤ ጋር አንድነት ፈጥረው ቱኬ ማማ የኦሮሞ ባላባት የኮምባልቾ ቀኛዝማች ሽቤ የሚቆ በመሆን ተባብረው በሕዝቦቹ መካከል ፀብም ሲፈጠር ያስማሙ /ያስታርቁ/ ነበር፡፡

ጥ. ስልጢ ባላባት ነበረው?

መ. ቀኛዝማች ሻምሮ የሚባሉ ባላባት ነበሩ

ጥ. የነሱም በቤተሰብ ነው ሲዋረድ የመጣው?

መ.　አዎ

ጥ.　የአንዱ ባላባት የሌላወን አይነካም?

መ.　አይነካካም ሁሉ በወሰኑ ብቻ ነው

ጥ.　ጂዶ ትክክለ ቦታው የት ነው?

መ.　በቤቡላ ዋናው የሻሸሜ መንገድ ላይ ነው ህፃናት አምባ

ጥ.　የሚራቆ ባላባት የት ነበር የሚቀመጡት?

መ.　እዚሁ ሚራቆ ቆሼ ነበር የሚኖሩት

ጥ.　ቆሼ ነበረች ዋና ከተማ የባላባት

መ.　ቆሼ ከ1940 እስከ 1944 አወራጃ ነበረች ሻለቃ አስፋው ገ/አምላክ አወራጃ አስተዳደሪ ቀኝአዝማች አፈወርቅ የፍርድ ቤት አዛዥ ቀኛ ሼቤ ሚኤቦ ዋና ባላባት በስራቸው 17 ጭቃ ሹም ነበራቸው

ጥ.　ደብዳቤ በማምጣት መሬት የወሰዱ ሰዎች ብዙ ናቸው እዚህ አካባቢ

መ.　አዎ ከ40 በላይ ይሆናሉ ብዙ ናቸው

ጊዜያችሁን ከኔ ጋር በማሆን ለሰጣችሁ ሚጃ አመሰግናለሁ፡፡